የቅንጅት(CUD) እና የሕብረት(UEDF) ጥምር የድጋፍ ኮሚቴ በኖርዌይ

በኖርዌይ የትግራይ ተወላጆች ስም ለወጣዉ መግለጫ የተሰጠ መልስ !!

ጁላይ 20, 2005

በኖርዌይ የቅንጅት(CUD) እና የሕብረት(UEDF) ጥምር የድጋፍ ኮሚቴ በኖርዌይ የትግራይ ተወላጆች ማሕበር ስም የወጣውን መግለጫ በተናጠልና በጋራ ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

በመግለጫዉ ተራ ቁ.1 ማንኛውም ፓርቲ የገዥውን ፓርቲ ፖሊሲም ሆነ አካሄድና አፈጻጸም በመንቀፍ የተሻለ አማራጭ ነው ያለዉን ለሕዝብ በማቅረብ ወደ ስልጣን ለመውጣት መሞከር ተገቢና ዴሞክራሲያዊ ሂደት መሆኑን እንድምታምኑ መግለጻችሁ እያስደሰተን ይህን የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት አቡጊዳ ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን ለ 14 ዓመታት በፈጸመው ግፍ ለፍርድ እንዳይቀርብ በመስጋት በጠብመንጃ አፈሙዝ ስልጣኑን ለማራዘም ወደቆረጠው መንግስት መልእክቱን እንድታቀኑ ትባቱን ይስጣችሁ እንላለን።

በተራ ቁ. 2 **"በምርጫዉ ሂደትና ቆጠራ ማጭበርበርና ጉድለት ካለ?"** በማለት በአርዮስ ትህትና የጥርጥር ሓረግ የጀመራችሁትን መግለጫ **"ሁሉም ፓርቲዎች በቅድመ ምርጫዉ በተሰማሙበት ሕጋዊ መድረኮች እርምት እንዲያደርግ መጣር ተገቢና ዴሞክራሲያዊ መሆኑን"** እንደምታምኑ በመጥቀስ መቋጨታችሁ የህወሓት እብሪት ድፍረትና ሌብነት ፣ ያስቆጣዉ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቱን በመጠቀም ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ለመንቀፍ ድፍረቱን ብታጡም እንድምታዉ የህወሓት መንግስት መግለጫ የገደል ማሚቶ በመሆን ከማስተጋባት ያለፈ መልእክት እንደሌለው እንገልጻለን።

በተራ ቁ 1. እና 2. ፊራ ተባ እያላችሁ የጀመራችሁት ይህ በኖርዌይ የትግራይ ተወላጆች ስም የወጣ መግለጫ እርቃኑን ወጥቶ ግልጽ የዘረኝነት መልእክቱን የከተበዉ በተራ ቁ. 3 ህወሓት/ኢህአዴግ እንደገዥ ፓርቲ **"ተቃዋሚዎች ስልጣን ላይ ከወጡ የትግራይ ተወላጆች ይታረዳሉ"** በማለት የሚያናፍሰውን ፍሬ-ከርስኪ የ'እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል' መንግስታዊ ፕሮፓጋንዳ ሳትጠቅሱ፣ የትግራይ ህጻናት በአይደር በሻእብያ ሲደበደቡ ከወገናቸዉ ከትግራይ ሕዝብ ጋር በመቆም በትግራይ ሕዝብ አድናቆት የተቸረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ለማጥፋት ባደረጋችሁት ከንቱ ሙከራ ነው። ዓላማችሁ በማያሻማ መንገድ በአለቆቻችሁ የተሰጣችሁን ትእዛዝ ለማስፈጸምና የዋህ የትግራይ ተወላጆችን በማደናገር የጌቶቻችሁን የሥልጣን ጊዜ ለማራዘም ስለሆነም አጥብቀን እናወግዘዋለን።

በተራ ቁ. 4. በኖርወይ የምንኖር ኢትዮጵያውያን በቋንቋ በሃይማኖትና በፖለቲካ አመለካከት ሳንለያይ በምንሰባሰብበት ማሕበር ቢሮ ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን በመጠቀም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ የህወሓት መሪዎች ቅልብ ጦር የጥይት ሰለባ ለሆኑት ወንድም እህቶቻችን የህሊና ጸሎት ሲደርግ **"ሲሰርቁ ነው የሞቱት እንነሳም!!"** በማለት እንዳልተመጻደቃችሁ ሁሉ ግፍን የፈሩ **አባሎቻችሁ "ጡር ፍሩ?"** ሲሏችሁ እምቢ እንዳላላችሁ አሁን በአርዮስ ትህትና የአዞ እምባ ለማፍሰስ መሞከራችሁ ማንነታችሁን እንደማይደብቅ እንገልጻለን።

"ከመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ያልተመጣጠነ እርምጃ የወሰዱ ካሉ?" በማለት በአጽንኦት ያሰመራችሁበት ሓረግ የድሃ የሰማእታት እናቶችን እምባ ሲቃና ጡር ሳትፈሩ አሁንም በድሆች ደም ለመሳለቅ መቁረጣችሁን ያሳያል። **"ባልዋሉበት የተጎዱ ወገኖች ካሉ?"** በማለት ያሰመራችሁበትና ይህን የህዝብ ሰላም ያደፈረሰ ሁኔታ ያደራጁ ሃይሎች ወደ ፍርድ እንዲቀርቡ ለጌቶቻችሁ ያስተላለፋችሁት ጥሪ **በሲቪክ ማህበር ስም የምትንቀሳቀሱ የህወሓት ጀሌዎች** መሆናችሁን ከማጋለጡ በስተቀር ፋይዳ እንደሌለዉ እንገልጻለን።

በመላዉ ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተቃዋሚ ድርጅት አባልነት ፣ ደጋፊነት ተደራጅተውና ሳይደራጁ የሕዝብ ሰቆቃና ብሶት ከንክንዋቸው በቋንቋና በሃይማኖት ሳይለያዩ፣ በማድረግ ላይ ያሉትን ሰላማዊ ሰልፍ ማውገዛችሁ ከቶውንም አይደንቀንም። ሰላማዊ ሰልፉ ያነጣጠረው በህጻን አራጁ መንግስት፣ በካድሬዎቹ ላይና በቅልብ ጦሩ ላይ ነበርና። ህወሓት በመላው

ዲያስፖራ ስውር ቆንስሎችና በህወሓት ተቃዋሚነት ስም በስደተኝነት የሚኖሩ ተልእኮ የተሰጣቸዉ ሰላዮች እንዳሰማራ አበክረን እናውቃለን። በዚህ ህዝባዊ አንድነት በተንጸባረቀበት ሰላማዊ ትግል የራደው ህወሓት የመጨረሻ የዘረኝነት ካርድ መዞ ህዝብ ከህዝብ ለማጋጨት መቁረጡንም እናውቃለን። ይህን መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ ለማራገብ መሞከራችሁን እየኮነንን ሙከራችሁ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብን በተለይ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ብልህነትና አስተዋይነትን እንደመሳደብ በመቁጠር ካነሳችሁት ሃሳብ ጋር ግንኙነት ባይኖረዉም **"የኢትዮጵያ ሕዝብ የአማራና የትግራይ ሕዝብ ብቻ እንዳልሆነ ልናስታውሳችሁ እንወዳለን !!"**

"እርዳታ እንዳይሰጥ ቀሰቅሳችኋል" ያላችሁትን አስመልክቶ ትናንት ለተሰጣችሁ ተልእኮ እንዲያመች እንደ ማሕበር ረድኤት ትግራይ የመሳሰሉ ድርጅቶች የነመለስ የሙስና ምንጭ እንደሆኑ ፣ እርዳታው በትክክል ለህዝብ እንደማይደርስና ለፖለቲካዊ ሥራም እንደሚውል በውስጥ አዋቂነት እንዳልመሰከራችሁ ሁሉ፣ ዛሬ አንድ እግሩ መቃብር የገባው መንግሥታችሁ እንዲያገግምበትና የሕዝቡን ሰላማዊ ትግል እንዲያፍን እርዳታ ለድሃዉ ህዝብ በትክክል መድረሱ ስይረጋገጥ እንዳይሰጥ የሚለውን የጋራ እቋማችን ለመቃወም መሯሯጣችሁን በጥብቅ እናወግዘዋለን።

በመጨረሻም በተ.ቁ. 6 በጣት የምትቆጠሩ ግለሰቦች ጥቂት የዋሕ የትግራይ ተወላጆችን በማስተባበር <u>በሲቪክ ማህበር ስም</u> ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን ስትደረድሩ ፣ ያላንዳች ሃፍረት በኖርዌይ የምንኖር ኢትዮጵያውያን (የትግራይ ተወላጆችንም ጨምሮ) ያካሄድነውን ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ <u>"የተወሰኑ ሰዎች!!"</u> በማለት ለማናናቅ ከሞከራችሁ በኋላ የ'በሬ ወለደ' ውሸት በማከል የሰላማዊ ሰልፋችን ማስታወቅያ ዘረኛ ይዘት እንደነበረው ብትገልጹም ፣ የመለስ ዜናዊ ቅልብ ጦር የንጹሃን ድሆችን ደም ማፍሰሱን በድጋሚ እያረጋገጥን ይህን መጥቀሳችን ነገ ፍትሕ ስትሰፍን ተጠያቂ የሚሆኑት ወንጀለኞቹ እንጂ ኢትዮጵያዊው የትግራይ ሕዝብ እንዳልሆነ የትግራይ ሕዝብ ስለሚረዳ ወንጀለኞችን በጉያው ለመደበቅ እንደማይፈቅድ ያለጥርጥር እናረጋግጥላችኋለን።

በሲቪክ ማህበር ስም በህወሓት ጀሌዎች ከሚመራዉ ማሕበር ቀንበር ስር ያላችሁ ጥቂት የዋህ የትግራይ ተወላጆችም ቀንበሩን በመስበር ማሕበራችሁን <u>ነጻ የሲቪክ ማህበር</u> ለማድርግ ትግላችሁ እንደሚቀጥል እናምናለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የትግል ወላፈን በህወሓት ጀሌዎች አይዳፈንም!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!!!!